የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሚያዚያ 15 ቀን 2000 ዓም

# የተጭበረበረው ምርጫና የተቃዋሚ ኃይሎች የትግል ምርጫ

የግንቦት 1997 ሽንፈት ከደረሰበት ወዲህ የወያኔ አገዛዝ ደም አፍሶም፣ ጨፍጭፎም አጭበርብሮም በሥልጣን ለመቆየት ከበፊቱም በበለጠና በከረረ ደረጃ የወሰነ በመሆኑ ምርጫ በሚለው ቧልት ለማጀብ መነሳቱ ስህተት መሆኑን ደግመን ደጋግመን የገለፅነውን በቅርቡ ተደረገ የተባለው የወያኔ የአካባቢና የማሟያ ምርጫ ሀቅነቱን አረጋግጦታል። ወያኔ በራሱ ከራሱ ተወዳድሮ ራሱን አሸናፊ ብሎ አፅድቋል። ታማኝ ተቃዋሚ የተባሉት በዚሁ ምርጫ ሊሳተፉ ቢሞክሩም በሩን ዘግቶና አፈናም አካሂዶባቸው ራሳቸውን ከምርጫው እንዲያገሉ አድርጓል።

ታማኝ ተቃዋሚ የተባሉት በምርጫው አንሳተፍም ማለታቸው አገዛዙን አለሸፋኝ አስቀርቶ ይበልጥ ፀረ ዴሞክራሲነቱን ያጋለጠ በመሆኑ አዎንታዊ እርምጃ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ለዚህ አገዛዝ ወዳጅ የሆኑ ክፍሎች ስለ ኬንያና ዚምባብዌ ምርጫዎች መዛባት ብዙ የተቃውሞ ጩኸት እያሰሙ፣ የወያኔን ዓይን አውጣ ማጭበርብር ግን በዝምታ ማለፋቸው እንዳለ ሆኖ ወያኔ ከተለጣፊዎቹ ጋር እርቃኑን መውጣቱ የሚካድ አይደለም። በኃይል ተጠቅሞ ሕዝብን በግድ በምርጫው ለማሳተፍ የሞከረውም ከሽፎበታል። በምርጫው የተሳተፈው ሕዝብ ቁጥር በጣም አነስተኛ መሆኑም ሊደበቅ ካለመቻሉ የተነሳ ምርጫ ከተባለው ሂደት በኋላ ለምን አልመረጣችሁም እያለ ሺዎችን ማፈሱና ማሰሩ ሌላ ማስረጃ ነው። የወያኔ አገዛዝ የምርጫ ህግ የሚለው በራሱ የተፃፈና ለራሱ የሚበጀው "ህግ" ከመሆኑ ሌላ የምርጫው ቦርድም ቢሆን የተሞላው በራሱ ሹመኞችና ታዛዦች ነው። በአጭሩ ነፃ ምርጫና ወያኔ መቸም ቢሆን መቼ፣ በመጠኑም ሆነ በትንሹ ሊጣጣሙ የሚችሉ አለመሆናቸውን ዳግም ለመገንዘብ ተችሏል። በመሆኑም ሀገር ወዳድ ተቃዋሚ ኃይሎች ከዚህ ተገቢውን ትምህርት ቀስመው የትግል ስልታቸውን በዚሁ መሰረት መቃኘትና ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል። ወያኔ ጋር ተቃቅፎና ተቻችሎ መኖር ይቻላል፣ የዴሞክራሲን በር ገርበብ አድርጎ ይከፍትልናል ወዘተ በሚልና መሰረተ ቢስ በሆነ መልክ በትጥቅ ትግል ስልት ላይም በመዝመት በአደናጋሪ ዘመቻ የተሳተፉትን ሁሉ ከንቱነትና አልፎም ቅጥረኛነት ማጋለጥና ወያኔ መቸም ቢሆን መች የሕዝብን ድምፅ ሊያከብር እንደማይችል ለአንዴም ለሁሌም መደምደም ያስፈልጋል።

ዳግም የተከሰተው የምርጫ ማጭበርበር ለተቃዋሚ ኃይሎች የሚሰጠው ትምህርት በወያኔ ምርጫ ቧልት ወደፊት ለመሳተፍ መነሳት ከስህተትም ያለፈ ስህተት መሆኑን ነው። ሕዝብ በወያኔ አገዛዙ ሆነ ምርጫ በሚለውም ላይ ቅንጣት ታህል ዕምነት የሌለው መሆኑን በግልፅ አሳይቷል። የደም ዋጋ የተከፈለበት ተመክሮአችን በወያኔ ላይ መለሳለስን ሳይሆን ማምረርን የግድ ይላል። አገዛዙ ወዳጅና ለነፃ ውድድር ተካፋይ ሳይሆን የሕዝብና የሀገር ጠላት ነውና ለመጪው ምርጫ ሳይሆን ለመጪው መራራ ፍልሚያ መዘጋጀቱ አማራጭ የሌለው ሆኗል። የተቃዋሚዎች የትግል ምርጫ ሕዝባዊ አመፅና ሁለገብ ትግልን ማፋፋም ብቻ ነው ሊሆን የሚገባው። ይህ የሆነበት ምክንያትም ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ሀገርን ለማዳን ሌላ መፍትሄና መንገድ ባለመኖሩ ነው። ይህን የትግል ምርጫ ለማክቸልቸልና ለወያኔ አገዛዝ መገዛትን በፊት ለፊትም ሆነ በረቀቀ መንገድ ለመስበክ የተነሱ ክፍሎች ማመፅን በማውገዝ፣ ብናምፅ ረዳት አይኖረንም፣ ዓለም የአንድ ኃያል መንግሥት ተገዢ ናትና እሱም ወያኔን ይደግፋልና፥ ፀጥ ብለን እንገዛ ወዘተ በሚል ትጥቅ ሊያስፈቱ ነጋ ጠባ ቢጥሩም ጠላቱን ለይቶ፣ የትግል ስልቱንም አውቆና ተባብሮ ለሚነሳ ሕዝብ ምንም የሚሳነው ወይም ሊወጣው የማይችለው ምንም ችግርና ዕንቅፋት ሊኖር እንደማይችል ግልፅ ነው። ስለዚህም የተቃዋሚ ኃይሎች ዋና ወቅታዊ

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com

ተግባር በወያኔ አገዛዝ ላይ ሕዝብ ተባብሮ እንዳይነሳ ጋሬጣ የሆኑትን በማሽነፍ ሕዝብን ለአመፅ ማደራጀትና መምራት ነው፡፡ የምርጫውን ባልትም ቢሆን የወያኔ አገዛዝ ከተለጣፊዎቹ ጋር እንዳይቀጥልም የሥልጣን ዕድሜውን ማሳጠር ያሻል፡፡

ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ ሊካሄድ የሚችለው የወያኔ አገዛዝ በሕዝብ ቆራጥ ትግል ሲደመሰስና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊተካ ሲችል ብቻ ነው፡፡ የሕዝብን ሉዓላዊነትና የሀገርን ደህንነት ለማስጠበቅ በቅድሚያ የወያኔን አገዛዝ በትግል መጣል ይገባል፡፡ በአመፅና በትግል እንጂ በወያኔ የበላይ ተቆጣጣሪነትና መልካም ፍቃድ በሚካሄድ ምርጫ ወያኔን ማሽነፍ የሚቻል አይደለም፡፡ የሕዝባችን ስርየትም ከባዕዳን በጎ ፍቃድና ድጋፍ የሚገኝ ሊሆን እንደማይችልም ዛሬ አከራካሪ አይደለም፡፡

**የወያኔን አገዛዝ በሕዝባዊ አመፅ ለማስወገድ ተባብረን እንነሳ!!**

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com